*4127 Redwood Road*
*Oakland, CA 94610*
*Tel: (510) 530 - 3681*

ሰኔ 1 ቀን 2002 ዓ/ም
ቁጥር 302/2010

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ላይ የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፥የሀገራችንን ወቅታዊ ችግርና በአሸባሪው በወያኔ አገዛዝ ዜጎች የዜግነትመብታቸው የተገፈፈበትን ድምጻቸውም በኃይል የተነጠቀበትን የማ ጭበርበር የምርጫ አፈጻጸምን አስመልክቶ የወጣ መግለጫ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ባሳለፈቻቸው ዘመናት ሁሉ በውጭ ወራሪ ኃይል፥ቀድሞ በጉዲት ዮዲትና በግራኝ አህመድ፣በመቀጠልም በድርቡሽና በፋሺሺት ጣሊያን፣የደረሰባት ችግር አሁን በዘረኛው የወያኔ አረመኔያዊ አስተዳደር ካደረሰባት ችግር ጋር ሲነጻጸር፥የአሁኑ የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከሁሉም እጅግ የባሰና የከፋ፥እስካሁንም ድረስ ገና ፈውስ ያልተገኘለት፥በዚህ ጊዜም ይረሳል የማይባል የታሪክ ጠባሳና ቁስል ነው።

ጥንታዊትና ታሪካዊት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ታፍራና ተከብራ የኖረች የውጭ ጠላትንም አሳፍራ ሕያው ታሪክን በማስመዝገብ በዓለም የታወቀች የጀግኖች ሀገር መሆንዋን ታሪክ የሚመሰክረው ሀቅ ነው። ዛሬ ግን በኢትዮጵያዊነት ስም በቅጥረ ኞች በንዳዎች በጥፋትና በሞት የገደል አፋፍ ላይ ትገኛለች።

ወያኔ በብሔራዊ የሕዝብ ምርጫ ስም ያደረገውን ዓይን ያወጣ ማጭበርበር፤ በስደት ላይ ያለው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ ይቃወማል። ይህ አደገኛ የወያኔ የአራዊት ባሕርይ የኢትዮጵያ ሀገራችንንም ሆነ የሕዝባችንን ሕልውና በጉልበት በመርገጥ ዜጎችን በማሸበር የሚፈጽመው እኩይ ተግባር በእጅጉ የሚያሳዝን ነው።

ወያኔ የሀገራችንን ጥንታዊ የታሪክ ገጽታ በመቀየር፥ሀገሪቱንም ያለወደብ በማስቀረት፥ ለዘመናት ተስማምቶና ተከባብሮ የኖረ ሕዝባችንን፥በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል፥የፈ ጸመው ታሪካዊ በደል አልበቃ ብሎት፤ እናቶችን በእስር ቤት በማጎር፣ሕጻናትን ያለ አሳዳጊ በማስቀረት፥ብዙዎችንም በጨለማ እስር ቤት በማጎርና በረኃብ አለንጋ በመቅ ጣት፥በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ንጹሃን ዜጎችን በማፈንና፥የወደፊት ተረካቢው ትውልድ ለነገ እንዳያስብ በፍርሃትና በጭንቀት በማሰቃየት፣የሀገሪቱን ክብርና ሉዓላዊነት ገፎ፥ መሬቷን ለርካሽ የፖለቲካ ተግባር ለባዕዳን በመሸጥ፤ይህ ሁሉ ከሀዲነቱ አልበቃ ብሎ ት፥አሁንም የጥፋት ዘመቻውን በበለጠ በማጠናከር፥የሕዝባችንን እና የሀገራችንን ጥፋ ት በማፋጠን ላይ ይገኛል።

ABBA MELKESEDEK ARCHBISHOP

ይህ በመሆኑም፥ወያኔ በብሔራዊ የሕዝብ ምርጫ ስም ያደረገውን ዓይን ያወጣ ክህደት ት፥በስደት ላይ ያለው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዋና ዋና ነጥቦች አውግዞታል።

1ኛ. ያሸባሪ ቡድን የሆነው ወያኔ በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ያለው በደል፥ በእጅጉ የሚያሳዝን ነው። በብዙ መገናኛ ብዙኃን እንደተረጋገጠው፥የኢትዮጵያን ሕዝብ «ሕይወትህን ወይም ፊርማህን» በሚል አጣብቂኝ ምርጫ እንዲገባ፥ተማሪውን ወያኔን ካልመረጥክ ከትምህርት ቤት ትባረራለህ፣ሠራተኛውንም ወያኔን ካልመረጥክ ከሥራህ ተወገዳለህ፥ከዚህም በላይ ሕይወትህን ወይም ፊርማህን፥በማለት በኃይል በማ ስገደድ ያለምንም የምርጫ መስፈርት ራሱን በብቸኝነትና በአምባ ገነንት በጥፋት መን በር ላይ በማስቀመጡ፣

2ኛ. የወያኔን ዓይን ያወጣ የማጭበርበር ተግባር፥በዓለም ያሉ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች በይፋ ተቃውመውታል። ወያኔ ግን ከሰው ልጅና ከዓለም ሕዝብ እውነተኛ ባሕርይ ጋር፥በመቃረን የጠብ መንጃ ኃይሉን ተማምኖ የሕዝባችንን የሰብአ ዊና የዜግነት መብት በፍጹም አምባ ገነንነት በመርገጡ፤

3ኛ. ወያኔ ለኢትዮጵያ የወደፊት ዘለቄታዊ ደኅንነት፥ለሕዝቦችዋም ተባብሮና ተከባብሮ የመኖርን ዋስትና ከማሰብ ይልቅ፥ሆን ብሎ ሀገሪቱ ወደ ዘርና የእርስ በርስ ጦርነት እንድታመራ፥ወደ ከፋ ውጥረት እየገፋት በመሆኑ፤

ከሀዲው ወያኔ ከዚህ በላይ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ የፈጸመውን የሀገርና የወገን ክህደት፥በደልና ግፍ፥ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ላይ የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕ ዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፥በጥብቅ አውግዞታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ለዘመናት መታወቂያህ ሆኖ የኖረው ጨዋነትህን፥ሰላም ወዳ ድነትህን፥ትዕግሥትህን ለዓለም አሳይተሃል! ያንተን የልብ ትርታ በማዳመጥ በሰላማዊ መንገድ አንተን ወክለው በተቃዋሚ የፖለቲካ መስመሮች ተደራጅተው የመሩህን የተ ቃዋሚ ድርጅቶች ቅዱስ ሲኖዶስ ያደንቃል። በአንድነት ሁነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል፥ለአንድነቱ፣ለደኅንነቱና፣ለክብሩ እራሳቸውን ለእስራት፥ለስቃይና ለውርደ ት፥ውድ ሕይወታቸውንም ሳይቀር አሳልፈው ለሰጡ ለኢትዮጵያ ልጆች የዘመናችን ሰማዕታት መባል ይገባቸዋል።

<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!</u>

የከሀዲውን የወያኔን ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ የምትሸከምበት ትከሻና አቅም የለህም። ጥበብህና እውቀትህ፥ጋሻህና መከታህ፥ኃይልህና አዳኝህ፥ ሁሉን ለማድረግ ሥላጣን ያለ ው አምላክህ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለ ሆነም አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍስህ፥በፍጹም አሳብህ፥በፍጹም ልብህ፥በፍጹም ኃይልህ ውደደው። ወደርሱም ብቻ በኅብረትና በአንድነት ሁነህ ዘወትር ጸልይና ተማጸን። ሁሉን ማድረግ የሚቻለውን አም ላክህን እውነተኛ መሪ አድርገህ በእምነትህ ጽና። በእርሱም ስም እንደ እውነተኞቹ አባቶችህ «እክህደከ ሰይጣን» ብለህ ወያኔን ክጄሃለሁ በለው። እንዲህ ያደረክ እንደ ሆነ አምላክህ እግዚአብሔር ከከሃዲው የወያኔ አረመኔያዊ አገዛዝ ነጻ ያወጣሃል።

የኢትዮጵያ አምላክ የጨለማውን አገዛዝ እድሜውን እንዲያሳጥረው፥ለሀገራችንም ቅን መሪን እንዲተካ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ዘወትር በጸሎት ያስብሃል።

ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅ! ሕዝቧንም ይባርክ!